የሳንባ ነቀርሳ፥ ለበሽተኛ የሚሰጥ መረጃ

የተላላፊ በሽታ ሃኪምች መረጃ ልሳን።

ይህ መረጃ ለምን ደረሰዎት?

ይህ መረጃ የደረሰዎት የሳንባ ነቀርሳ በሽታ ያለብዎት ወይም ይኖርብዎ ይሆናል ተብሎ ስለተጠረጠረና ተገቢውን ህክምና እንዲያደርጉ ነው። ይህ ቅጽ ስለ ሳንባ ነቀርሳ በሽታ፣ ከበሽታው እንዴት እንደሚድኑ እና እርስዎ ምን ማድረግ እንዳለብዎ የሚያስረዳ መረጃ ይዟል።

ሳንባ ነቀርሳ ምንድን ነው?

ሳንባ ነቀርሳ (TBC ወይም TB የሚባለው) *"Mycobacterium tuberculosis"* በመባል በሚታወቀው የሳንባ ነቀርሳ ባክቴሪያ የሚፈጠር የበሽታ ዓይነት ነው። በአብዛኛው ግዜ ባክቴሪያው የሳንባ ንዳድ ወይም መበከል የሚያመጣ ሲሆን ሌሎች የሰውነት ክፍሎችን፣ ለምሳሌ እጢዎችን፣ የሳንባ ከረጢትን፣ አጽምን፣ አንጎልን እና ኩላሊትን ሁላ ይነካል። በሽታው ከያዘ በኋላ ምልክቱ (Symtom) ለረጅም ግዜ - ማለትም ወራትና ዓመታት ሊቆይ ይችላል። በህጻናትና የበሽታ መከላከል አቅማቸው ዝቅ ያለ ሰዎች ላይ፥ በሽታው በፍጥነት ሊከሰት እንደሚችል ሁሉ ለከፋ ችግርም ሊዳርግ ይችላል።

የሳንባ ነቀርሳ እንዴት ይተላለፋል?

በሽታው ሳንባ ነቀርሳ፡ በሳንባው ውስጥ ባለ ሰው አማካይነት ይተላለፋል። አንድ ሳምባ ነቀርሳ ያለበት ሰው፥ ቤት ውስጥ ሲስል፣ ሌላው ሰው ያንን ዓየር ሲስብ ባክቴሪያ ያዘለ በጣም ጥቃቅን ጠብታዎችን ወደ ሳንባው ያስገባል። ሳንባ ነቀርሳ በዋናነት የሚተላለፈው ከበሽተኛው ጋር በሚደረግ የቅርበትና የረጅም ግዜ መነካካት ነው። በዚህ የተነሳ በአንድ መኖሪያ ቤት ውስጥ የሚኖሩ ሰዎች፥ በበሽታው ለመለከፍ የተጋለጡ ይሆናሉ። ወላጆች ወደ ልጆቻቸው እንደሚያስተላልፉ ሁሉ ወደ ቅርብ ባልንጀሮቻቸውም ማስተላለፍ ይችላሉ። በሽታው በአጭር ግዜ ግንኙነት እምብዛም አይተላለፍም፣ ለምሳሌ በሥራ ቦታ እና በትምህርት ቤት ውስጥ በሚደረግ ግንኙነት የመተላለፍ ዕድሉ አነስተኛ ነው።

ሳንባ ነቀርሳ እንዳለብዎት በምን ይታወቃል?

በሰፊው የሚታወቅባቸው ምልክቶች፥ የክብደት መቀነስ፡ ረዘም ላለ ግዜ የሚቆይ (ሶስት ሳምንታት በላይ) የማሳል ሁኔታ፣ በሌሊት በላብ የመዘፈቅ ችግር እና ትኩሳት ናቸው። የህመሙ ዓይነት የነቀርሳው ባክቴሪያ እንደሚገኝበት የሰውነት ክፍል ይለያያል። ሌሎቹ የህመም ዓይነቶች (ነቀርሳው እጢ ላይ ከሆነ) እብጠት ወይም (ነቀርሳው አጽም ወይም ሆድ ላይ ከሆነ) ደግሞ የሚጠዘጥዝ ዓይነት ህመም ይሰማል።

የሳንባ ነቀርሳ ምልክቶች እንደየ ታማሚው ሰው በሰፊው ይለያያል፥ ማለትም ከምንም ህመም እስከ ከባድ ችግር የሚያስከትል ጠንቅ ድረስ ነው።

ሳንባ ነቀሳ እንዴት ይተላለፋል?

ሳንባ ነቀርሳ የያዛቸው ሰዎች ማለትም፣ የሚስሉት ነጠብጣብ ተመርምሮ ባክቴሪያ የተገኘባቸው ሰዎች፣ እስኪታከሙ ድረስ በሽታውን በከፍተኛ ደረጃ ማስተላለፍ ይችላሉ። ይሁን እንጂ ህክምና በጀመሩ የመጀመሪያው ሳምንት ውስጥ በሽታውን የማስተላለፍ አቅማቸው በእጅጉ ይቀንሳል። ነቀርሳው ከሳንባቸው ውጭ፣ በሌላ የሰውነት ክፍል ላይ ያለባቸው ሰዎች በሽታውን ማስተላለፍ አይችሉም። ሳንባ ነቀርሳ ያለባቸው ትንንሽ ልጆች ከሞላ ጎደል በሽታውን ፈጽሞ ማስተላለፍ አይችሉም። ሳንባ ነቀርሳ በልብስና በሌሎች እቃዎች በኩል ሊተላለፍ አይችልም። በሽታው ከቤት ውጭ እምብዛም አይተላለፍም።

ሳንባ ነቀርሳ አደገኛ ነውን?

ሳንባ ነቀርሳ ህክምና ካልተደረገበት ባክቴሪያው ወደ ሌላው የሰውነት ክፍል ተዛምቶ ጉዳት ሊያደርስ ይችላል። በህክምና ያልመከነ ሳንባ ነቀርሳ ከባድ የጤና ችግር ሊያስከትል ከመቻሉም ባሻገር እስከ ሞት ሊያደርስም ይችላል። ትንንሽ ልጆችና በሽታን የመከላከያ አቅማቸው የተዳከመ ሰዎች፥ በሳንባ ነቀርሳ በሽታ በከባዱ ሊጠቁና ሊታመሙ ይችላሉ።

ሳንባ ነቀርሳ እንዴት ይድናል?

የሳንባ ነቀርሳ በሽታ የሚፈወሰው በሽታውን የሚፈጥረው ባክቴሪያን የሚገድል መድሃኒት በመውሰድ ነው። ህክምናው ረጅም ግዜ የሚወስድ ሲሆን በብዙ ወራት ውስጥ የሚካሄድ ነው። ህክምናውን ሃኪም ባዘዘው መሠረት መውሰድ በጣም ያስፈልጋል። አንዳንድ መድሃኒቶች በባዶ ሆድ መወሰድ ይኖርባቸዋል፣ አብዛኛውን ግዜ አንድ ሰዓት ያህል ግዜ ከቁርስ

በፊት። ህክምናው በሚወሰድበት ግዜ ከታዘዙት ክኒኖች ውስጥ ምንም መዝለል አያስፈልግም። የሃኪሞን ምክርና ትዕዛዝ መከተል ያስፈልጋል። መድሃኒት አወሳደዱ በታዘዘው መሠረት ካልተከናወነ ባክቴሪያው መድሃኒቱን የመለማመድና የመቋቋም አቅም ስለሚፈጥር፣ በመካያው በሽታውን ለመፈወስ አስቸጋሪ ሁኔታ ይፈጠራል። የሳንባ ነቀርሳ መድሃኒት የሚሰጠው በነጻ ነው፣ የህክምና ክትትሉ እንዲሁ ነጻ ነው።

የበሽታ መተላለፊያውን ዱካ መከተል – ምን ማለት ነው?

የሳንባ ነቀርሳ ያለባቸውን ሰዎች ፈልጎ ማግኘትና ህክምና እንዲከታተሉ ማድረግ በጣም ጠቃሚ ነው፣ ምክንያቱም ከላይ እንደተጠቀሰው ለከፍተኛ ጉዳት ከመዳረግ ስለሚያድን፣ እንዱሁም በሽታው ወደ ሌላ ሰው እንዳይጋባ ስለሚያደርግ ነው። ስለዚህ ሳንባ ነቀርሳ የያዛችሁ ሰዎች፣ ከነ ማን ጋር በቅርበት ኖራችሁ እንደነበር ወይም ተገናኝታችሁ እንደነበር ወይም በሽታውን ማን ላይ አስተላልፋችሁ ኣንደሆን ወይም ማን ወደ እርሶ እንዳስተላለፈ መናገር ይኖርባችኋል። አንድ ሰው በሽታው ሊኖርበት ይችላል ሆኖም ግን ህመም ላይሰማው ይችላል።

ሳንባ ነቀርሳ የተላላፊ በሽታዎች ሕግ ውስጥ ተካትቷል – ምን ማለት ነው?

ሳንባ ነቀርሳ ካለብዎት፣ አኗኗርዎ በሽታውን ወደ ሌላ ሰው የማስተላለፍ አጋጣሚ በማይኖርበት ሁኔታ መሆን አለበት። የሳንባ ነቀርሳ ያለብዎት ወይም ይኖርብዎት ይሆናል ተብለው የሚጠረጠሩ ከሆነ፣ **ሃኪምዎ የሰጥዎትን የራስ አያያዝ መመሪያ በሚገባ መከተል** ይኖርብዎታል፡-

- ተላላፊ ሳንባ ነቀርሳ ካለብዎት፡
  - ለተወሰነ ግዜ ሃኪም ቤት ገብተው ህክምና እንዲከታተሉ ሊገደዱ ይችላሉ።
  - ወደ ሥራ ወይም ትምህርት ቤት ወይም የዕረፍት ግዜ ማሳለፊያ ቦታ በሚሄዱበት ግዜ፣ ሃኪምዎ በሽታውን ወደ ሌላ ሰው ማስተላለፍ አይችሉም ብሎ እስኪነግርዎት ድረስ፣ መመሪያውን ይተገብራሉ።
- ሃኪምዎ ተመልሰው እንዲጎበኙት ከነገርዎት በቀጠሮው መሠረት መገኘት ይኖርብዎታል።
- መኖሪያ ቤትዎን ከቀየሩ፣ ይህንኑ ሃኪምዎ እንዲያውቅ ማድረግ አለብዎት።
- የበሽታውን መተላለፊያ ዱካ በመከተሉ ሥራ እንዲተባበሩ ያስፈልጋል።

ራስዎን እንዴት እንደሚይዙ የሚገልጽ መመሪያ ከተሰጥዎትና እዚያ ላይ ስህተት መስሎ የሚታይዎት ነገር ካገኙ፣ በሚኖሩበት ክልል የሚገኘውን የተለላፊ በሽታ መከላከያ ሃኪምን (smittskyddsläkaren) ያነጋግሩ።

የበለጠ ማወቅ ከፈለጉ?

ሳንባ ነቀርሳን በተመለከተ ተጨማሪ መረጃ እነዚህ ድረገጾች ላይ ያገኛሉ
www.1177.se
www.folkhalsomyndigheten.se

የሚገናኙት ሰው አድራሻና ቴሌፎን (Kontaktuppgifter)

የጤና ጣቢያው ሥም *(Namn på mottagningen)*

……

ያገኙት ሰው ሥም(Du har träffat)

ሃኪም *(Läkare)*……..

ነርስ *(Sjuksköterska)* ……

የጤና ጣቢያው ቴሌፎን ቁጥር *(Telefonnummer/telefontid till mottagningen)*

……